ሴት አድርጎ የፈጠራቸውና የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት በጋብቻ ያጣመራቸው እግዚአብሔር ስለ ሆነ፣ እርሱ ስለ ጋብቻ፣ ወሲብና ቤተሰብ የሚለውን ማወቅ በጣም አስፈላጊያችን ነው። በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክራለን፡-

ሀ. ለጋብቻ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

ለ. ለባሎችና ሚስቶች የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

ሐ. ስለ ወሲብ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

መ. ለክርስቲያኖች ቤተሰባዊ ሕይወት የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

ሠ. ከአንድ በላይ ስለ ማግባት ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው?

ረ. እግዚአብሔር ስለ ፍቺ ምን ይላል?

ሰ. የትዳር ጓደኛ ስለ መምረጥ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች ምንድን ናቸው?

ሸ. ክርስቲያን ባለትዳሮች የመካንነትን ችግር እንዴት ይወጣሉ?

## ሀ. ለጋብቻ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

### ጋብቻ የእግዚአብሔር አሳብ ነበር

ከመጀመሪያው ጋብቻ የእግዚአብሔር አሳብ ነበር። ጋብቻ የሰው አሳብ አልነበረም። ጋብቻን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ለአብሮነት፣ ለፍቅር፣ ለጋራ ማበረታቻ፣ ለተግባራዊ እርዳታና ለወሲባዊ እርካታ የሚኖረውን ፍላጎት ለማርካት ያቀደው ውጥን ነበር (ዘፍጥ. 2፡18፤ 1 ቆር. 7፡2-3)። በሕይወት ዘመናቸው በሙሉ አንዳቸው ለሌላቸው በጋብቻ በተሳሰሩ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በተፈጠረ ደኅንነትና ፍቅር ውስጥ ልጆች እንዲወለዱና እንዲያድጉ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር [መዝ. (127)፡3፤ ሚል. 2፡14-16፤ ማቴ. 19፡6]።

እግዚአብሔር አዳምን በዔድን ገነት ውስጥ ሲፈጥር፣ ፍጹም ሰው አድርጎ ፈጥሮታል። ይሁንና፣ ለአዳም አንድ ነገር ያስፈልገው ነበር። እግዚአብሔር፣ «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤

የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» ብሏል (ዘፍጥ. 2:18)። እግዚአብሔር ለአዳም ፍጹም አጋር ለመፍጠር ወሰነ። ለአዳም የሌላ ሰብአዊ ፍጥረት ኅብረት ያስፈልገው ነበር። እግዚአብሔር ሌሎቹን ፍጥረታት ወንድና ሴት አድርጎ ፈጥሮአቸው ነበር (ዘፍጥ. 6:19)። አዳም ወንድ ስለ ነበረ፥ እግዚአብሔር ከአዳም የጎድን አጥንቶች አንዱን በመውሰድ የሴት ጓደኛ አበጀለት። ይህንንም በማድረግ፥ እግዚአብሔር ለአዳም በሕይወት ዘመኑ ሁሉ አብራው የምትኖር ጓደኛና ለጋብቻውም ፍሬያማነት የወሲብ አጋር ሰጠው። በአዳምና ሔዋን ሥጋዊ ውህደት፥ እግዚአብሔር የሰው ዘር እንዲቀጥል ዐቀደ (ዘፍጥ. 1:27-28፤ ዘፍጥ. 2:24)።

### ጋብቻ - በሰብአዊ ማኅበረሰብ የመጀመሪያው ተቋም

እግዚአብሔር ጋብቻን የመሠረተው ከሌሎች የሰው ልጆች ተቋሞች ሁሉ በፊት ነበር። ይህም ጋብቻ የሰው ልጅ ማኅበረሰብ መሠረት እንደ ሆነ ያሳየናል። ጋብቻ የተመሠረተው ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ነበር። ይህም የጋብቻን ቅዱስነት ያሳየናል።

እግዚአብሔር በጋብቻ ደስ ይለዋል። በቃና ዘገሊላ በነበረው የሰርግ በዓል ኢየሱስ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ የለወጠበት ተአምር (ዮሐ. 2:1-11)፥ እግዚአብሔር ሰዎች በጋብቻ ሙሉ ደስታ እንዲኖራቸው እንደሚፈልግ ያሳያል። ወንዶችና ሴቶች ፍቅርንና ተቀባይነትን እንዲለማመዱና ምሉዓን እንዲሆኑ ይሻል። ጋብቻ የተሠራው ለዚህ ዓላማ ነው።

በእግዚአብሔር ዕቅድ፥ ጋብቻ ግብረ-ገባዊና ማኅበረሰባዊ ጽናት ላለው ኅብረተሰብ መሠረት ነው። ይህም እግዚአብሔር ዝሙትን (ዘጸ. 20:14)፥ ወሲባዊ ግድፈትን (1 ተሰ. 4:3-6)፥ የቤተ ዘመድ የፈቃደ-ሥጋ ግንኙነትን (ዘሌ. 18 ከቁጥር 6 ጀምሮ) እና ግብረ ሰዶምን (ሮሜ 1:24-28) የሚጠላበት ዋነኛው ምክንያት አካል ነው። እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔር ለጽኑ ሰብአዊ ማኅበረሰብ የወጠነውን ዕቅድ ያኮላሻሉ፤ ያጣምማሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል» በማለት ያስጠነቅቀናል (ዕብ. 13:4)።

ዛሬ ብዙ ማኅበረሰቦች ማኅበራዊና ግብረ-ገባዊ ብልሹነት ውስጥ ከሚዘፈቁበት ምክንያት ከፊሉ፥ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ሳይጠብቁ

ለመኖር በመወሰናቸው ነው። የሚያሳዝነው የወሲብ ኃጢአቶች የከፉ ውጤቶች የሚያስከትሉ መሆናቸው ነው። ከእነዚህም የከፉ ውጤቶች ሁለቱ የፍችና የፈራረሱ ቤቶች በከፍተኛ ደረጃ መጨመርና ዓለም አቀፋዊ የኤድስ መቅሠፍት ናቸው።

ጋብቻ በዓለም ለሁሉም ሰዎችና ለሁሉም ባህሎች እግዚአብሔር ያቀደው ነው (ዘፍጥ. 2፡24፤ 12፡3፤ ማቴ. 19፡3-9)። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በወጠነው ዕቅድ ቤተሰብ በሌላ በማንኛውም ተቋም ሊተካ አይችልም። አንድ ሰው የቤተሰብን ሕይወት ቢያበላሽ፥ እግዚአብሔር ለጠቅላላው የሰው ዘር በወጠነው ዕቅድ ውስጥ ጣልቃ መግባቱ ነው። በዔድን ገነት የመጀመሪያውን ጋብቻ የመሠረተው እግዚአብሔር ነበር (ዘፍጥ. 2፡21-25)። ጋብቻን በራሳቸው ምግባረ-ብልሹነትና አለመታመን ያበላሹት ሰዎች ናቸው።

ለጋብቻ የእግዚአብሔር ዕቅድ

የእግዚአብሔር ዕቅድ አንድ ወንድ አንዲትን ሴት እንዲያገባ ነው። እግዚአብሔር ለፈጠረው ወንድ አንዲት ሴት ፈጥሮለታል (ዘፍጥ. 2፡22-24)። ይህ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚገኘው አጋርነት ለሕይወት ዘመን ሁሉ እንዲቆይ ፈለገ። በማቴዎስ 19፡5-8 ኢየሱስ፥ «ስለዚህ ሰው እናቱንና አባቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል . . . እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው» ብሏል። ይህ የዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን ለብዙ ምክንያቶች አስፈላጊ ነው።

በመጀመሪያ፥ ጋብቻ ለሚስት በሕይወት ዘመኗ ሁሉ እንክብካቤ፥ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች አቅርቦትና ዋስትና ይሰጣታል (ቆላ. 3፡12-13፤ 1 ጴጥ. 3፡7)። ሁለተኛ፥ ለስሜታዊ ደኅንነትና ልጆችን ለማሳደግ አስፈላጊ ነው። ልጆች እግዚአብሔር እንደሚፈልገው እንዲያድጉ ከተፈለገ፥ አስተማማኝና የተረጋጋ አካባቢ ያስፈልጋቸዋል። ወላጆች ሲለያዩ ወይም ሲፋቱ፥ ልጆች በከፍተኛ ስሜታዊ ሥቃይ ይጠቃሉ። እግዚአብሔር ጋብቻን ከመሠረተበት ዓላማ ከፊሉ፥ ልጆች በመንፈሳዊ ሁኔታ የሚያድጉበትን እርጋታና ፍቅር የተመላበት አካባቢ መስጠት ነው። ሚልክያስ 2፡15፥ «እግዚአብሔር . . . የሕይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድር ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ፥ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል» ይላል።

እግዚአብሔር በሕይወት ዘመኑ ሁሉ አንድ ወንድ አንዲት ሴት እንዲያገባ ያቀደበት ሌላው ምክንያት፥ ከሴቲቱ የስሜት ደኅንነት ጋር ይዛመዳል። አንዲት ሴት ባሏ እርሷን ብቻ እንደሚያፈቅር ማወቅ ያሻታል። ወንድ ብዙ ጋብቻ በሚፈጽምበት ቤት የሴት ስሜታዊ መሻቶች ሊሟሉላት አይችሉም። አንድ ሰው ከአንድ የሚበዙ ሚስቶች ካሉት፥ ሁልጊዜም በሚስቶቹ መካከል ቅንዓትና ጥላቻ ይኖራል። በእግዚአብሔር ፊት ወንዶችና ሴቶች እኩል ናቸው (ገላ. 3፡28)። ለሚስት የባሏን ሥጋዊ መሻቶች ማሟላት እንደሚገባት ሁሉ፥ ለባልም የሚስቱን ስሜታዊ መሻቶች ማሟላት አስፈላጊ ነው።

## ከአንድ በላይ ማግባት የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም

በፍጥረት እግዚአብሔር ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት ስለ ሰጠ፥ የብዙ ጋብቻ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ከአንድ በላይ ጋብቻ መልካም ጅማሬ አልነበረውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው የመጀመሪያው ብዙ አግቢ (ላሜሕ) ነፍሰ-ገዳይም ነበር (ዘፍጥ. 4፡23)። ይሁንና፥ ከአንድ በላይ ጋብቻ እንደ ዝሙት አይደለም። በብዙ ጋብቻ ባል ሚስቶቹንና ልጆቻቸውን የመቀለብ ኃላፊነት አለበት። በብዙ የአፍሪካ ጥንታዊ ባህሎች ዘንድ የብዙ ጋብቻ የተለመደ ነገር ነው።

እንደ ንጉሥ ዳዊት በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው አያሌ ሰዎች ብዙ ሚስቶችን አግብተው ነበር። አንዳንድ ሰዎች የብዙ ጋብቻን በአፍሪካ ፍትሐዊ ለማድረግ ይህንኑ እውነት ይጠቀማሉ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች ለዓላማው ቢጠቀምም፥ ብዙ ሚስቶች እንዲያገቡ አልፈለገም ነበር። ነገሥታትን በተመለከተ እግዚአብሔር፥ «ልቡም እንዳይስት ሚስቶችን ለእርሱ አያበዛም» ብሏል (ዘዳ. 17፡16-17)። እውነቱ ሲታይ፥ እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳን ባለ ብዙ አግቢዎችን፥ ብዙ ሚስቶች በማግባታቸው በውጤቱ እንዲሠቃዩ አድርጓል። ይህ በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ሊታይ ይችላል (ዘፍጥ. 16፡1-6)።

አጋርን ሁለተኛ ሚስት አድርጎ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ፥ አብርሃም በቤቱ ደስታ አልነበረውም። በአጋርና በሣራ፥ በይስሐቅና በእስማኤል መካከል ቀናተኛነት ነበር። በይስሐቅና በእስማኤል እንዲሁም በተጣይ ትውልዶቻቸው መካከል የተነሣው ቅንዓትና ጥላቻ እስከ ዛሬ ድረስ ለ4000 ዓመታት ቀይቷል። ይህም በአይሁዶች (የይስሐቅ ዘሮች) እና በዓረቦች (የእስማኤል ዘሮች) መካከል በሚካሄደው ጥላቻ ውስጥ ሊታይ

ይችላል። ወደ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚታየው የብዙ ጋብቻ ችግር ተጨማሪ ማብራሪያ እናቀርባለን።

## የእግዚአብሔር ዕቅድ በጋብቻ ውስጥ ለሚኖር አንድነት

በእግዚአብሔር ዕቅድ፥ ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ሦስት ገጽታ ያለውን አንድነት ያካትታል። ይህ ባለ ሦስት ገጽታ አንድነት፥ ሥጋ፥ አእምሮ፥ መንፈስ ተብሎ ከሚገለጸው የሰብአዊ ፍጥረታት ባለ ሦስት ገጽታ ተፈጥሮ ጋር ይዛመዳል (1 ተሰ. 5:23፤ ዕብ. 4:12)።

### 1. ሥጋዊ አንድነት

እግዚአብሔር ለጋብቻ ባቀደው ነገር ውስጥ የመጀመሪያው አንድነት፥ የወሲባዊ ግንኙነት ሥጋዊ አንድነት ነው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሴቲቱን ወደ ወንዱ ሲያመጣት፥ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ሆነው አይተፋፈሩም ነበር (ዘፍጥ. 2:25)። ጌታ፥ «ስለዚህ ሰው እናቱንና አባቱንና ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» ብሏል (ዘፍጥ. 2:24)። መጽሐፍ ቅዱስ ሥጋዊ የጋብቻ ጥምረት በእግዚአብሔር ፊት መልካምና የተቀደሰ እንደ ሆነ ያስተምራል (ዘፍጥ. 1:27-28፥ 31፤ ምሳሌ 5:18-19፤ ዕብ. 13:4)።

ከጋብቻ ሥጋዊ አንድነት ልጆች ከመወለዳቸውም በላይ፥ ለቤተሰቡ የጋራ ኃላፊነት ይመሠረታል። ባል ቤተሰቡን ለመመገብ የመሥራት ኃላፊነት አለበት (ዘፍጥ. 2:15)። ሚስት ልጆችን የመውለድና ቤቱን የመንከባከብ ኃላፊነት አለባት (1 ጢሞ. 5:14)።

### 2. አእምሮአዊ እና ስሜታዊ አንድነት

እግዚአብሔር ለጋብቻ በወጠነው ዕቅድ ሁለተኛው ዓይነት አንድነት፥ አእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነት ነው። አእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነት የሚመጣው ሁለት ሰዎች በኅብረትና በስምምነት ሲኖሩ ነው። ለዚህ ዓይነቱ አንድነት፥ ባልና ሚስት ቢያንስ የተወሰኑ የጋራ እሴቶች፥ የጋራ ዓላማዎችና የጋራ ፍላጎቶች ሊኖሩአቸው ይገባል። የልጆች መወለድ እነዚህን የጋራ እሴቶች፥ ዓላማዎችና ፍላጎቶች ለማዘጋጀት ይረዳል። አንድ ዓይነት ቋንቋና ባህል ለአእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነት እገዛ ያደርጋል። የዚህ ዓይነቱ አንድነት ነው የሰዎችን የኅብረት፥ የተቀባይነትና የእሴት መሻቶች የሚያሟላው።

በዓለም ሁሉም ሰው በሌላ ሰው ሊፈለግ፥ ሊወደድና ሊደነቅ ይፈልጋል። እንዳልተፈለገና ዋጋ እንደሌለው ሆኖ የሚሰማው ሰው የመኖር ዓቅም አይኖረውም። በአእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነት ለማደግ፥ ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው ለመጫወትና አሳቦችን ለመጋራት ጊዜ መውሰድ አለባቸው። አንዳንድ ነገሮችን በጋራ ለማከናወንና ለአጋራቸው የሚያሻውን ነገር ለማሟላት ጊዜ መውሰድ አለባቸው (ፊልጵ. 2፡4)። በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን የአንድነት መታጣት ችግር በተመለከተ፥ ጳውሎስ፥ «የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፥ ምሕረትና ርኅራኄ ቢሆኑ ደስታዬን ፈጽሙልኝ፤ በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ» ብሏል (ፊልጵ. 2፡2)። ይህ የአእምሮአዊና የስሜታዊ አንድነት መግለጫ ነው። ምንም እንኳ ጳውሎስ በዚህ ዓረፍተ ነገሩ በጋብቻ ውስጥ ስለሚኖር አንድነት እየተናገረ ባይሆንም፥ የዚህ ምንባብ እውነታ ለጋብቻ ግንኙነትም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ሊዛመድ ይችላል።

ባልና ሚስት አእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነት ለማሳደግ በትዕግሥት የማይጠብቁ ከሆነ፥ ብዙም ሳይቆይ ይራራቃሉ። እርስ በርሳቸው ብዙም እንደማይቀራረቡ ሲሰማቸው፥ ጋብቻቸውም ደስታ እየተለየው ይሄዳል። ይህም ሥጋዊ ግንኙነታቸውን ይጎዳል። ባል ሚስቱን እንደ ሰብአዊ ፍጥረት በመመልከት በእርሷ ደስ መሰኘቱን ሳያሳይ ሲቀር፥ ሚስት ከባሏ ጋር የወሲብ ግንኙነት ለመፈጸም አትፈልግም። ለታመመ ጋብቻ መድኃኒቱ ባል ሚስቱን በእጮኝነታቸው ጊዜ ያደርግ እንደ ነበረው ማፍቀር፥ መንከባከብ፥ ማክበርና ትኩረት ሰጥቶ ማስተናገድ ነው። ይህ በኤፌሶን 5፡25 «ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ» የሚለው ምንባብ ትርጉም አካል ነው።

### 3. መንፈሳዊ አንድነት

እግዚአብሔር ለጋብቻ በወጠነው ዕቅድ ሦስተኛው ዓይነት አንድነት መንፈሳዊ አንድነት ነው። ይህ ሁለቱም ባልና ሚስት ክርስቲያኖች በመሆን ጌታን ለመከተል ሲፈልጉ የሚገኝ አንድነት ነው። እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ መንፈሳዊ አንድነትን ስለሚፈልግ አንድ ክርስቲያን ክርስቲያን ያልሆነውን ሰው እንዲያገባ በፍጹም አይፈልግም። መጽሐፍ ቅዱስ «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ። የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?» ይላል (2 ቆሮ. 6፡14-15)።

1. ባል ሚስቱን ከራስ ወዳድነት በጠራ መንገድና ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የሚወደውን ያህል መውደድ አለበት (ኤፌ. 5:25)። ይህም ራስን መሠዋትንና ራስን መካድን ይጠይቃል።

2. መልካሙ እረኛ ኢየሱስ ሕዝቡን በየዋህነት እንደሚመራ ሁሉ ባል ሚስቱንና ልጆቹን በየዋህነት መምራት አለበት [መዝ. (23)፤ ኤፌ. 5:23]። ይህ በዓለም እንዳለው የአምባገነንነት መሪነት ሳይሆን ራስን የመካድ የባርነት መሪነት ነው። ብዙ ባሎች ሚስቶቻቸውን በአምባገነንነት በማስተዳደር በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ላይ የሚመጣውን የእግዚአብሔር በረከት ያቅባሉ።

3. ባል ለቤተሰቡ የሚያስፈልገውን ማሟላት አለበት። ይህም ለማኅበራዊ፥ ስሜታዊና መንፈሳዊ ብሎም ሥጋዊ መሻታቸው የሚያስፈልገውን ነገር ማሟላትን ይጨምራል [መዝ. (23):1፤ 1 ጢሞ. 5:8]።

4. ባል ቤተሰቡን መንከባከብ አለበት (ኤፌ. 5:28-29)። እያንዳንዱ አባት የኢዮብን ምሳሌነት በመከተል በየዕለቱ ለሚስቱና ለልጆች መጸለይ አለበት (ኢዮብ 1:5)።

5. ባል ሚስቱን ማክበር አለበት (1 ጴጥ. 3:7)።

6. ባል ሚስቱን ማነፅ እና በክርስቶስ ማበረታታት አለበት (ኤፌ. 5:26).

7. ባል ሚስቱን በአሳብ እንደሚረዳት ማሳየት አለበት (1 ጴጥ. 3:7)።

8. ባል ልጆቹን ለማሠልጠን፥ ለማረም፥ ለመቅጣት እና በመንፈስዊ መንገድ ለማስተማር ኃላፊነት መውሰድ አለበት (ኤፌ. 6:4)። ይህ በቤት የባል የመሪነት ኃላፊነት ነው። በፍርድ ቀን ለቤተሰቡ መንፈሳዊ ሁኔታ እግዚአብሔር በኃላፊነት የሚጠይቀው ባልን እንጂ ሚስትን አይደለም። ይህም በዔድን ገነት ለተፈጸመው ኃጢአትና ዓመፀኛነት ሔዋንን ሳይሆን አዳምን በኃላፊነት ከጠየቀበት ሁኔታ ይታያል (ሮሜ 5:12,15, 18-19)።

የእግዚአብሔር ዕቅድ ለሚስት

ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን መውደድና ለእርሱም መገዛት ይኖርባታል (ኤፌ. 5:24)። በዚህ ማብራሪያ ቤተክርስቲያን ሚስት ልትከተላት የሚገባት ምሳሌ ናት።

1. በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ወንዶችና ሴቶች እኩል ስለ ሆኑ (ገላ. 3:28)፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወንዶችና ሴቶች ለክርስቶስ ካላቸው ፍርሃት የተነሣ አንዳቸው ለሌላቸው ሊገዙ ይገባል (ኤፌ. 5:21)። ይህም እርስ በርሳቸው ለጠባያቸው ተጠያቂዎች መሆን አለባቸው ማለት ነው። ይህ በጋብቻ ግንኙነትም በሚስቶችና ባሎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

በወንዶችና ሴቶች መካከል ከሚኖረው ከዚህ አጠቃላይ ግንኙነት በተጨማሪ እግዚአብሔር በፈጠራቸው ተቋማት ሁሉ እንደ ሆነው በጋብቻም ውስጥ የተዋረድ ሥርዓት አለ። በእግዚአብሔር የተዋረድ ሥርዓት ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ ሁሉ፥ ባልም የቤተሰቡ ራስ ነው (ኤፌ. 5:23)። ይህንኑ ፈለግ በመከተል ሚስት ልክ ለክርስቶስ እንደምትገዛው ለባሏ መገዛት አለባት (ኤፌ. 5:22-24)። ይሁንና ይህ የተዋረድ ሥርዓት ንጉሥ በጭፍሮቹ ላይ እንደሚያደርገው፥ ባል ሚስቱን ለመጨቆንና ለመደብደብ የሚያስችለውን መብት አይሰጠውም። በሌላ በኩል መጽሐፍ ቅዱስ የዚህን አሳብ ተገላቢጦሽ ያስተምራል። ባል ሚስቱንና ቤተሰቡን የሚመራበት መንገድ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚወዳትና እንደሚመራት ሁሉ፥ በመሥዋዕትነት በመሠዋት አገልግሎትና ራስን በሚክድ ፍቅር ተለይቶ መታወቅ አለበት (ኤፌ. 5:25)።

2. ሚስት ባሏን ልታበረታታና ልትረዳ ይገባል። ሚስት ባሏን ከምታበረታታባቸው እጅግ አስፈላጊ መንገዶች አንዱ ለእርሱ መጸለይ ነው (ዘፍጥ. 2:18)።

3. ልጆች ትወልዳለች (1 ጢሞ. 2:15)።

4. ሚስት በቤት ጣፋጭ መንፈስ ሆና መቆየት አለባት (1 ጴጥ. 3:3-4)።

5. ሚስት ቤተሰቧን በጥሩ ሁኔታ መያዝ አለባት (ምሳሌ 31:37)።

6. ሚስት መልካም ምስክርነት ሊኖራት ይገባል (ምሳሌ 31:31፤ ቲቶ 2:3)። ይህም ድሀን ለመርዳት እጅ መዘርጋትን ይጨምራል (ምሳሌ 31:20)።

7. በዕድሜ የገፉ ሚስቶች ሴት ልጆቻቸውን ጨምሮ ወጣት ሴቶች ባሎቻቸውን እንዲወዱና እንዲያከብሩ በመንፈሳዊ መንገድ ሊያስተምሯቸው ይገባል (ቲቶ 2:4)።

የእግዚአብሔር ዕቅድ ለባልና ለሚስት እንደ ወላጆች

እግዚአብሔር ወላጆች ሁሉ ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ ሊከተሉት የሚገባ ምሳሌ ነው (ኤፌ. 5:1-2)። በትንሽ ልጅ አእምሮ ስለ እግዚአብሔር የሚታሰበው የመጀመሪያ አሳብ ብዙውን ጊዜ የወላጆች በተለይም የአባት ምስል ነው።

1. ወላጆች ክርስቶስን በመምሰል በልጆቻቸው ፊት የመንፈሳዊ አኗኗርን ምሳሌ መቅረጽ አለባቸው (ኤፌ. 5:1-2)። ልጆች ከወላጆቻቸው ምክር ይልቅ ምሳሌአቸውን ወደ መከተሉ ያዘነብላሉ።

2. ልክ እግዚአብሔር ወላጆችን እንደሚወድ ወላጆች ልጆቻቸውን መውደድ አለባቸው (ኤፌ. 5:2)።

3. ወላጆች ልጆቻቸውን ስለ እግዚአብሔር መንገዶች ማስተማር አለባቸው (ምሳሌ 1:7-8)። ይህ በተለይ ትክክለኛና ትክክለኛ ስላልሆኑ፥ መልካምና ክፉ አሳቦች፥ እንዲሁም መሠረታዊ ስለ ሆኑ ግብረገባዊና መንፈሳዊ እሴቶች ሊነገራቸው ይገባል። ክርስቲያን ወላጆች የልጆቻቸውን ግብረገባዊና መንፈሳዊ ሥልጠና ለባህላዊ መሪዎች ወይንም ለመንግሥት ት/ቤቶች መርሐ ግብሮች መተው የለባቸውም። እግዚአብሔር ወላጆች ልጆቻቸውን ስለ ሕግጋቱና ስለ መንገዶቹ እንዲያስተምሯቸው ይፈልጋል (ዘዳ. 6:6-7)።

4. ልክ እግዚአብሔር በፍቅር እንደሚቀጣን ወላጆች ልጆቻቸውን በፍቅር መቅጣት አለባቸው። ይህ የአባት ኃላፊነት ነው (ኤፌ. 6:4፤ ዕብ. 12:9)።

5. ልክ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን እንደሚሰጥ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ማሟላት አለባቸው [መዝ. (23):1፤ 1 ጢሞ. 5:8]።

6. እግዚአብሔር እኛን እንደሚጠብቀን ወላጆች ልጆቻቸውን በሥጋዊ፥ በአእምሮአዊና በመንፈሳዊ ሁኔታዎች መጠበቅ አለባቸው [መዝ. (18):2፤ (144):2]።

7. እግዚአብሔር እኛን እንደሚመራን ወላጆች ልጆቻቸውን መምራት አለባቸው [መዝ. (32):8]።

### ሐ. ስለ ወሲብ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር ሰዎችን ሲፈጥር ለወሲባዊ እርካታ ዓላማ ወንድና ሴት አድርጎ ፍጥሮአቸዋል (ዘፍ. 1:27-28)። ለክርስቲያኖች ወሲብ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በጎነትና ደስታ ያሰበው ነገር እንደ ሆነ መረዳት መልካም ነው። ወሲብ በጋብቻ ውስጥ ሲፈጸም ኃጢአት አይደለም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ወሲብ መልካምም (ዘፍጥ. 1:31) ቅዱስም ነው (ዕብ. 13:4)። ወሲብ ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት በዔድን ገነት የተሰጠው ነው (ዘፍጥ. 1:27-28፤ 2:21-25)። መጽሐፍ ቅዱስ «ምንጭህ ብሩክ ይሁን፤ ከጕብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ። እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተዋበችም ሚዳቋ፥ ጡትዋ ሁልጊዜ ታርካህ፥ በፍቅርዋም ሁልጊዜ ጥገብ» ይላል (ምሳሌ 5:18-19)።

የመጀመሪያው የሰው ኃጢአት አዳም ከሚስቱ ጋር ወሲብ መፈጸሙ እንደ ሆነ በስፋት ይታመናል (ዘፍጥ. 4:1)። ይህ ግን ሐሰት ነው። የመጀመሪያው ኃጢአት እግዚአብሔር መልካምና ክፉ ከምታስታውቀው ዛፍ እንዳይበላ የተሰጠውን ትእዛዝ የመተላለፍ ተግባር ነበር (ዘፍጥ. 2:17፤ 3:6)።

ከኃጢአት የተነሣ ሰው እግዚአብሔር ለወሲብ የወጠነውን ዕቅድ አጣሟል። በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት ወሲባዊ ግንኙነትን ባልና ሚስት በጋብቻ ቃል ኪዳን ውስጥ ብቻ እንዲፈጽሙት በጥብቅ የተደነገገ ነው (1 ቆሮ. 7:2-5፤ ዕብ. 13:4)። ወሲብን ከጋብቻ ውጭ መፈጸም የከፋ ኃጢአት ነው። ዛሬ በዓለም ውስጥ ብዙ ችግሮች በኃጢአት ከሚፈጸም ወሲብ የመነጩ ናቸው። እንደ ዝሙት፥ ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም የወሲብ ግንኙነት፥ ግብረ ሰዶም (በተመሳሳይ ፆታዎች መካከል

የሚደረግ ግንኙነት)፥ በቤተሰብ አባላት መካከል የሚደረጉ ፆታዊ ግንኙነቶች፥ ከእንስሳት ጋር የሚፈጸሙ ወሲባዊ ክንውኖች ሌሎችም አጸፋ ልምምዶች ለእግዚአብሔር ርኩሰት ናቸው። በዘሌዋውያን 18 እና 20፥10-21 እግዚአብሔር ንጹህ ያልሆኑትንና የከፋ ቅጣት የሚያስከትሉትን ልምምዶች ዝርዝር ይሰጠናል።

ወሲብ እንደ እሳት ኃይለኛ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት መንገድ የተነሣ እሳትን መቋቋም ይቻላል። እሳት በጣም ሊጠቅመን ይችላል። ምግባችንን ለማብሰልና ቤታችንን ለማሞቅ ልንጠቀምበት እንችላለን። ይሁንና ቤት በእሳት ከተቀጣጠለ ቤቱን ሊያወድምና በውስጡ ያሉትን ሰዎች ሊገድል ይችላል። ወሲብም እንዲሁ ነው። ወሲብን መቋቋም የሚቻለው እግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶችን ከፈጠረበት መንገድ የተነሣ ነው። በእግዚአብሔር ምሪት ውስጥ ወሲብ እግዚአብሔር ለተጋቡ ሰዎች ከሰጣቸው በረከቶች አንዱ ነው። ታላቅ እርካታ የሚገኝበትና ልጆችን ወደ ዓለም ለማምጣት የሚረዳ መሣሪያ ነው። የእግዚአብሔርን ምሪት ከጣሱ ግን ወሲብ ቤትን እና የሰውን ሕይወት ሊያጠፋ ይችላል።

ሰዎች የወሲብ ፍላጎታቸውን ከጋብቻ ውጭ ለማርካት ሲሞክሩ ጋብቻ ይፈራርሳል፤ ቤተሰብ ይታመሳል፤ የግለሰቦችም ሕይወት ከእግዚአብሔር የፍርድ እርግማን በታች ይወድቃል። እግዚአብሔር ለኃጢአት ይቅርታ ያደርጋል ማለት በዚህ ሕይወት የኃጢአቱ ውጤቶች አይከተሉንም ማለት አይደለም። ይልቁንም ውጤቶቹ እጅግ የከፋ ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ ሰው ሌላውን በከፍተኛ ንዴት ተነሣሥቶ ቢገድልና በኋላ በከፍተኛ ጸጸት ንስሐ ቢገባ እግዚአብሔር ይቅር ሊለው ይችላል። ይሁንና ንስሐና ይቅርታ የሞተውን ሰው አያስነሡትም። ንጉሥ ዳዊትን በተመለከተ፥ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ከኦሪዮን ሚስት ጋር የፈጸመውን የዝሙት ኃጢአት ይቅር ቢለውም፥ የቤተሰቡ ሕይወት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተበላሽቷል (2 ሳሙ. 12:11-13)።

አንዳንድ ባህሎች ከጋብቻ በፊት የሚፈጸመውን ዓይነት የተወሰኑ ወሲባዊ ኃጢአቶች አይኮንኑም። አንድ ክርስቲያን ከእንደዚህ ዓይነት ባህል የመጣ ከሆነ፥ እንዲህ ዓይነቱን የወሲብ ግድፈት የኮነነው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ማወቅ አለበት። ክርስቲያን ለጠባዩ የሚጠየቀው በባህሉ ሳይሆን በእግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔር ሕግጋት ፍጹማን በመሆናቸው፤ ከባህል ጋር ለማጣጣም ብሎ አይለውጣቸውም።

ስለ ተበላሸ የወሲብ ግንኙነት ጥቂት ማለት አለብን። ዛሬ በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች፡ ብዙ ሰዎች ወደ ግብረ ሰዶም ፊታቸውን መልሰዋል። ይህ እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረበትን መንገድ ሙሉ ለሙሉ ማበላሸት ነው። እንስሳት እንኳ ወንዶችና ሴቶች ሆነው ተፈጥረዋልና ዛሬ ግብረ ሰዶማውያን ልምዳቸው ተገቢና አማራጭ የሕይወት ዘይቤ እንደ ሆነ ለመሟገት ይፈልጋሉ። እውነታው ግን እንደ እነዚህ ዓይነት ልምምዶች ለእግዚአግሔር ርኩሰት መሆናቸው ነው (ዘሌ. 20:13)። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ወሲባዊ ብልሹነትን ሲከተሉ እግዚአብሔር ለኃጢአታቸው አሳልፎ እንደሚሰጣቸውና በሕይወታቸው ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንደሚያመጡ ይናገራል (ሮሜ 1:24፥ 26)። እግዚአብሔር ጥንታዊዎቹን የሰዶምና ገሞራ ከተሞች በወሲባዊ ብልሹነት ኃጢአታቸው ሙሉ ለሙሉ እንዳወደማቸው ልብ ልንል ይገባል (ዘፍጥ. 19:1-25)። እግዚአብሔር ዛሬም አልተለወጠም።

ለግብረ ሰዶማዊ ሰው ትክክለኛ የክርስቲያን አመለካከት ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁልጊዜም ለግብረ ሰዶምና ለሌሎች የኃጢአት ልምምዶች ባሪያ ለሆኑት ሰዎች ፍቅር፥ ትዕግሥትና ርህራሄ ሊያሳዩ ይገባል። ክርስቲያኖች ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች እርዳታንና በክርስቶስ የሚገኘውን የመላቀቂያ ምክር ሊለግሷቸው ይገባል። በተመሳሳይ ጊዜም፥ ክርስቲያኖች ይህ ብልሹ ልምምድ ምንም እንዳልሆነ፥ ወይም ይኸኛው የሕዝቦች ቡድን ልዩ መብቶችን ሊያገኝ እንደሚገባ የሚሰነዝረውን አሳብ ሊታገሡ አይገባም። ይህና ሌሎችም የወሲብ ኃጢአቶች በእግዚአብሔር ኩነኔና ቁጣ ሥር ናቸው (1 ተሰ. 4:3-6)።

## የምኞት ችግር

ምኞት የሚታየው የሰዎች ተገቢ ፍላጎቶች በኃጢአት በመበላሸታቸው ነው። ፍላጎቶች በራሳቸው ክፉ አይደሉም። ፍላጎታችን እግዚአብሔር ከፈጠረን ሁኔታ ይመጣል። ለምሳሌ፥ እግዚአብሔር ሰዎች ሕይወትን ለማቆየት እንዲመገቡ አድርጎ ፈጥሮአቸዋል። ሰው ሲርበው የመመገብ ፍላጎት ቢያሳይ ኃጢአት አይደለም። ይሁንና፥ ከመጠን በላይ መመገብ ለምግብ ከሚኖረን ተገቢ ፍላጎት ያለፈ ብልሹ ተግባር ነው። ይህ የምኞት ዓይነት ነው።

እግዚአብሔር ወንዶችንና ሴቶችን እርስ በርሳቸው ከሚኖራቸው ተፈጥሮአዊ፥ ሥጋዊና ስሜታዊ ስበት ጋር ፈጥሮአቸዋል። ያ ስበት ኃጢአት አይደለም። ወደ ተቃራኒ ፆታ መሳብ የመጀመሪያው

የእግዚአብሔር ፍጥረት አካል ሲሆን፥ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ውስጥ ሁሉም መልካም እንደ ሆነ ገልጾአል (ዘፍጥ. 1:31)።

ችግሩ እግዚአብሔር የሰጠን ወሲባዊ ፍላጎት በኃጢአት መበላሸቱ ነው። ከዔድን ገነቱ ውድቀት ጀምሮ፥ ሰዎች ፍላጎታቸውን ጨምሮ በሁሉም የባሕርያቸው አካል ተበላሹ። ከኃጢአተኛ ተፈጥሮአቸው የተነሣ፥ ወንዶችና ሴቶች እግዚአብሔር እንዳቀደላቸው በጋብቻ አጋሮቻቸው አይረኩም። ይልቁንም፥ ሌላውን ወንድ ወይም ሴት በምኞት ይከተላሉ።

ፍቅር ወይስ ምኞት?

ብዙ ወጣቶችን የሚያስጨንቀው አንደኛው ጥያቄ በፍቅርና በምኞት መካከል የሚገኘው ልዩነት ነው። ሁለቱም ፍቅርና ምኞት ከፍተኛ የወሲብ ፍላጎትን ያካትታሉ። ልዩነታቸው ምንድን ነው? ፍላጎቱ ፍቅር ወይም ምኞት መሆኑን ለመወሰን አንድ ሰው ሊጠቀምበት የሚችለው ቀላል ሙከራ፥ ራስ ወዳድ ያለመሆን ሙከራ ነው። አንድ ወንድ አንዲትን ሴት በመንፈሳዊ ፍቅር ከወደዳት ለእርስዋ በሚኖረው ፍላጎት ራስ ወዳድ አይሆንም! የሚወዳትን ልጅ ከጋብቻ በፊት እንድትገናኘው በማደፋፈር አያሳፍራትም፥ ወይም አያረክሳትም።

ይህ መመሪያ የንጉሥ ዳዊት ልጅ የነበረው አምኖን በአባት በኩል እህቱ በሆነችው በትዕማር ላይ በፈጸመው የአመንዝራነት ተግባር ታሪክ ውስጥ በግልጽ ይታያል (2 ሳሙ. 13:1-12)። ትዕማር አስፈላጊ ከሆነ አምኖንን ለማግባት ፈቃደኛ ብትሆንም፥ አምኖን ግን ፍላጎቱን ለማርካት እስከ ጋብቻው ዕለት ለመጠበቅ አልፈለገም ነበር (2 ሳሙ. 13:13-14)። አምኖን ለትዕማር የነበረው የራስ ወዳድነት ፍላጎት ፍቅር ሳይሆን ምኞት ነበር። በሌላ በኩል፥ አናጺው ዮሴፍ ማርያምን ሚስቱ አድርጎ በመውሰድ ወሲባዊ ግንኙነት ከመፈጸሙ በፊት ለእርሙኛነት ዓመትና ለኢየሱስ ልደት ሲል በቆይታ ለመጠባበቅ ፈቃደኛ ነበር (ማቴ. 1:24-25)። ዮሴፍ ለእርስዋ እውነተኛ ፍቅር ስለ ነበረውና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ስለ ፈለገ፥ ማርያምን በትዕግሥት ለመጠበቅ ፈቃደኛ ነበር። በፍቅርና በምኞት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ፍቅር ለመስጠት ሲፈልግ፥ ምኞት ግን ለማግኘት ይሻል።

ፍቅር ራስን መካድ ሲሆን፥ ምኞት ራስን ማገልገል ነው።

ፍቅር የእግዚአብሔርን ጊዜ በትዕግሥት ለመጠባበቅ ሲፈቅድ፥ ምኞት ግን ለመጠበቅ አይፈቅድም።

ፍቅር ለተፈቃሪዋና ለልጆቿ የዕድሜ ልክ ኃላፊነት ለመውሰድ ሲፈቅድ፥ ምኞት ከወሲብ ጋር የሚሄደውን ኃላፊነት ለመሸከም አይፈልግም።

ፍቅር የተፈቃሪውን ደስታና በጎነት ሲሻ፥ ምኞት እርካታን ብቻ ይፈልጋል።

ፍቅር ለተወደደው ሰው ከቶውንም ኃፍረት የማያስከትል ሲሆን፥ ምኞት ግን ለሌላው ኃፍረት ቢያመጣም ግድ የለውም።

ፍቅር ለሕይወት ዘመን ሁሉ የሚቆይ ሲሆን፥ ምኞት ግን ጊዜያዊ ነው።

ፍቅር ከእግዚአብሔር የሚመጣ ታላቅ በረከት ሲሆን፥ ምኞት ትልቅ የኃጢአት እርግማን ነው። ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ የታዘዘ ሲሆን (ኤፌ. 5:25)፥ ከምኞት እንድንሸሽ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል (2 ጢሞ. 2:22)።

ፍቅር ሁሉንም ሲፈውስና ሲረዳ፥ ምኞት ሁሉንም ይጎዳል።

ፍቅር ደስታን፥ ሐሤትንና ሙላትን ሲያመጣ፥ ምኞት ሐዘንን፥ መራርነትንና ኃፍረትን ያስከትላል።

የፍቅር ጅማሬ የእግዚአብሔር ቅዱስ ባሕርይ ሲሆን፥ የምኞት ጅማሬ የሰው የኃጢአት ተፈጥሮ ነው።

የምኞት ችግር ላጤዎች ብቻ የሚጋፈጡት ሳይሆን፥ ብዙውን ጊዜ ባለትዳሮችም የሚታወኩበት ነው። ለባለትዳሮች አንደኛው ከምኞት የማምለጫ መንገድ መደበኛ የፈቃደ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ነው (1 ቆሮ. 7:3-5)። በብዙ የአፍሪካ ባህሎች፥ ልጅ ከተወለደ በኋላ ለሁለት ዓመታት ወይም ከዚያ ለሚበልጡ ጊዜያት ሚስቶች ከባሎቻቸው ጋር የፈቃደ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ አይፈልጉም። ይህ ብዙ ወንዶችን ወደ ምኞትና ዝሙት ስለሚመራ፥ መልካም አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ (ፈቃደ-ሥጋን) አትከላከሉ! ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈትናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ» ይላል (1 ቆሮ. 7:5)።

ሚስት ከወሊድ በኋላ ወዲያው አረግዛለሁ በሚል ፍርሃት ከባሏ ጋር የወሲብ ግንኙነት ለማድረግ ካልፈለገች፥ ከባሏ ጋር ሆና በቤተሰብ ምጣኔ ላይ ጠቃሚ ሀሳብ ሊሰጡ የሚችሉትን ክርስቲያን ሐኪሞች ማማከር ይኖርባታል። በቅድስና መውለድ ቤተሰቡንና ጋብቻውን ራሱ በብዙ መንገዶች ይረዳል።

አንዳንድ ባሎች ሚስቶቻቸውን በማፍቀር ፋንታ ምኞታዊ እርካታ ለመፈጸም ስለሚፈልጉ፥ የሚስቶቻቸውን ስሜት ይጎዳሉ። እግዚአብሔር ባሎች ሚስቶቻቸውን ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚወዳት አድርገው እንዲወዱአቸው አዝዞአል (ኤፌ. 5:25)፤ ይሁንና፥ ከምኞት ይርቁ ዘንድ አስጠንቅቆአቸዋል (2 ጢሞ. 2:22)። ይህም ባሎች በተለይም በወሲባዊ ግንኙነት ለሚስቶቻቸው ታላቅ ትዕግሥትና የዋህነትን ማሳየት አለባቸው ማለት ነው። ከጋብቻ በኋላም ቢሆን፥ ልክ ከጋብቻ በፊት ያደርግ እንደ ነበረው ለሚስቱ ፍቅር፥ ቸርነትና ትዕግሥት የሚያሳይ ሰው ደስተኛ ሚስት ይኖረዋል። ሚስቱን ከራስ–ወዳድነት በራቀ መንፈስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ለመውደድ ከፍተኛ ጥረት የሚያደርግ ወንድ ሚስቱ የበለጠ ምላሽ ስትሰጠውና ስትወደው ይመለከታል። ባሎች መኃልየ መኃልይ በምዕራፍ 4:1-5:4 የሚገኘውን ታሪክ ማንበብ አለባቸው፤ በዚህም ታሪክ ከብዙ ጊዜ በፊት አንድ ባል በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ለሚስቱ ያለውን ፍቅር እንዴት እንደ ገለጸ እንመለከታለን።

ላገቡ ሰዎች የምኞት ችግር በጣም ትልቅ ሊሆን ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህንን ፈተና ለመቀነስ ሊረዱ የሚችሉ ሁለት መመሪያዎች አሉ። የመጀመሪያው መመሪያ ክርስቲያኖች ዓይኖቻቸው ይመለከቱ ዘንድ በሚፈቅዱት ነገር ሁሉ ራሳቸውን መግዛት እንዳለባቸው ነው። በተለይም ወንዶች ለሚመለከቱት ነገር ስሜታውያን ናቸው። ንጉሥ ዳዊት ቤርሳቤህ ገላዋን ስታትጠብ በማየቱ ከእርሷ ጋር ዝሙት ፈጽሞአል (2 ሳሙ. 11:2)። ኢዮብ፡ «ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ፤ እንግዲህስ ቆንጆይቱን እንዴት እመለከታለሁ?» ብሏል (ኢዮብ 31:1)። ኢየሱስ፡ «ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል» ብሏል (ማቴ. 5:28)። ክርስቲያኖች ምን ዓይነት መጽሐፍ እንደሚያነቡ፥ ምን ዓይነት ፊልሞችና ሥዕሎች እንደሚመለከቱ መጠንቀቅ አለባቸው።

ሁለተኛው መመሪያ ከሥጋዊ ዳሰሳ ጋር የተያያዘ ነው። ሰውን መዳሰስ የወንዶችንና የሴቶችን የወሲብ ስሜት ስለሚቀሰቅስ ወደ ከፋ

ፈተና ሊወስድ ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ ወንድ ሴትን ባይነካት እንደሚሻል ይናገራል (1 ቆሮ. 7:1)። ወንዶች ከወጣት ሴቶች ጋር በሚሆኑበት ጊዜ ራሳቸውን ሊገዙ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እህቶቻቸው አድርገው እንዲመለከቱአቸው ይናገራል (1 ጢሞ. 5:1-2)። ለሰው ሚስቱ ካልሆነች ሴት ጋር በስውር ስፍራ መገኘት መልካም አይደለም።

### መ. ለክርስቲያኖች ቤተሰባዊ ሕይወት የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

1. የክርስቲያን ጋብቻ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ሊኖራት የሚገባውን ግንኙነት ለማሳየት ምሳሌ ሆኖ አገለግሏል (ኤፌ. 5:25-32)። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሁሉ ባልም ሚስቱን ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታና በፍጹም መሥዋዕትነት መውደድ አለበት (ኤፌ. 5:25)። ሚስትም ለክርስቶስ እንደምትገዛ ሁሉ ለባሏም መገዛት አለባት (ኤፌ. 5:22)። እነዚህ ሁለቱም ኃላፊነቶች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው።

2. የወላጆች ልጆችን የማሳደግ ተግባር ለልጆቻቸው በጌታ መንገዶች ደንበኛ የክርስቲያን ትምህርት መስጠትን ያካትታል (ዘፍ. 18:19፤ ኤፌ. 6:1፥ 4)። በዘዳግም 6:6-7 ጌታ፥ «እኔም አንተን የማዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው» ይላል።

ልጆችን የማሠልጠንና የማስተማር ድርሻ እግዚአብሔር ለወላጆች የሰጠው ኃላፊነት ነው። ምሳሌ 1:8፥ «ልጄ ሆይ፥ የአባትህን ምክር ስማ፥ የእናትህንም ሕግ አትተው» ይላል። እግዚአብሔር ቤት ለልጅ የደህንነት፥ የፍቅር፥ የእንክብካቤ፥ የፍላጎቱ ማሟያ፥ የሥልጠናና የፍቅር መቅጫ እንዲሆን ይፈልጋል። ጌታ በጳውሎስ በኩል፥ «አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው» ብሏል (ኤፌ. 6:4)። ቤተሰብ ልጆች በትክክለኛው መንገድ ያድጉበት ዘንድ በእግዚአብሔር የታቀደ ልዩ ስፍራ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡ እርሱን የሚያውቁና የሚታዘዙ ልጆች እንዲያሳድጉ ግድ ይለዋል (ዘዳ. 4:40፤ 5:29)።

3. ክርስቲያን ወላጆች ለልጆቻቸው ፍላጎት የመጠንቀቅ ኃላፊነት አለባቸው። ይህም እንደ ምግብ፥ ልብስና ሕክምና የመሳሰሉትን ሥጋዊ ፍላጎቶች ይጨምራል። እንዲሁም፥ ለፍቅርና ለደኅንነት የሚኖሯቸውን ስሜታዊ ፍላጎቶች ያካትታል። የፍቅርና የደህንነት ፍላጎት በሙላት የሚገኘው፥ ወላጆች እርስ በርሳቸው በሚዋደዱበትና በአንድነት በሚኖሩበት ቤት ነው።

## ሠ. ከአንድ በላይ ስለ ማግባት የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው?

ከአንድ በላይ ማግባት በአፍሪካ የከፋ ችግር ነው። ከአንድ በላይ ማግባት የጋብቻን ቃል ኪዳንና ኃላፊነቶች ስለሚያካትት፥ እንደ አመንዝራነት ወይም ዝሙት አይደለም። በአፍሪካ ማኅበረሰብ ከአንድ በላይ ማግባት በመደገፍ የሚነሡ ጠንካራ ሙግቶች አሉ፡–

1. በአፍሪካ ባህላዊ ማኅበረሰቦች ዘንድ ብዙ ሚስቶችን ማግባት ለአያሌ ምዕተ ዓመታት የኃይል፥ የሀብትና የዝና ተምሳሌት ሆኖ ቆይቷል። ምናልባት በብሉይ ኪዳን ነገሥታት አያሌ ሚስቶችን የሚያገቡት ለዚሁ ይሆናል። በጥንቱ ዓለም እጅግ ባለጸጋ የነበረው ንጉሥ ሰለሞን 700 ሚስቶችና 300 ቁባቶች ነበሩት (1 ነገሥት 11:3)። ይሁንና፥ የሰለሞን ብዙ ሚስቶች በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለውድቀት ዳርገውታል (1 ነገሥት 11:3-5)።

2. በባህላዊ ኅብረተሰብ፥ ሰው የቤተሰቡን ስም ወደሚቀጥሉት ትውልዶች ማስተላለፉ አስፈላጊ ነው። ብዙውን ጊዜ አያሌ ሚስቶችን ማግባት ስሙን ለመቀጠል ብዙ ወንዶች ልጆች እንዲኖሩት ዋስትና ይሰጣል።

3. የቤተሰብን ስም ከመቀጠሉ ጋር በቅርብ የተያያዘው አሳብ፥ ብዙ ልጆችንና የልጅ ልጆችን በመውለድ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ለረዥም ጊዜያት እንደሚታሰብና እንደሚከበር ነው። በባህላዊ ኅብረተሰብ ውስጥ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው።

4. በእርሻ ሥራ በሚተዳደሩ ኅብረተሰቦች ዘንድ፥ ብዙ ሚስቶችን ማግባት፥ ለግብርና፥ ለከብት እርባታና ለቤት ውስጥ ሥራ የሚያስፈልጉትን አያሌ ልጆች ለማፍራት ያስችላል። ይህም አንድ ሰው በሚታመምበት ጊዜ እንደሚሆነው፡ ችግር ሲያጋጥም አስፈላጊውን እርዳታ

መስጠትን ያጠቃልላል። ብዙ ቤተሰቦች የሚገኙበት ማኅበረሰብ የጥንካሬ ምልክት ተደርጎ ይታያል።

5. በብዙ የአፍሪካ ማኅበረሰቦች ከወሊድ በኋላ እስከ ሁለት ዓመታት ድረስ ሚስቶች የፊታደ-ሥጋ ግንኙነት ስለማይፈጽሙ፥ ብዙ ሚስቶችን ማግባት ባል የዝሙት ተግባር እንዳይፈጽም ያደርጋል።

6. የአፍሪካ ባህል በጣም ጠንካራ የማኅበረሰብ እሴቶች ስላሉት፥ ብዙ ሚስቶችን ማግባት ሰፊ ቤተሰብን ይመሠርታል፤ ይህም በሕይወት ደስታንና ትርጉምን እንደ መጨመር የሚቆጠር ነው።

7. አንድ ሰው ብዙ ሴት ልጆችን ከወለደ፥ በጋብቻ ወቅት ከጥሎሽ በሚገኘው ገንዘብ ሀብቱ ይዳብራል።

8. በብዙ ነገዶች ለጤና ልጅ አልባ ሴት መሆን እጅግ ከፉ እንደ ሆነ ይታመናል። ከዚህም የተነሣ፥ ብዙ የአፍሪካ ሴቶች ላጤ ከመሆን ይልቅ ከአያሌ ሚስቶች አንዷ መሆንን ይመርጣሉ። በተጨማሪም፥ በላጤነት የምትኖር ሴት የዝሙት ምክንያት በመሆን በማኅበረሰቡ ላይ ኃፍረት እንደምታመጣ የሚገልጽ አሳብ አለ።

9. ከአንድ በላይ ማግባት አንድ ወላጅ ብቻ ያላቸውን እናቶች ችግር ያቃልላል።

10. ብዙ ሚስቶችን ማግባትና የብዙ ልጆች መኖር ሰውየው በሽምግልናው እንደሚጦር ያረጋግጥለታል።

እነዚህ የመሟገቻ ነጥቦች እንደሚያመለክቱት፥ ከአንድ በላይ ጋብቻ ከባህላዊ የአፍሪካ አመለካከት አንጻር ተገቢ ይመስላል። ይሁንና፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከአንድ በላይ ጋብቻ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆነ በግልጽ ያስቀምጣል። ምንም እንኳን ከአንድ በላይ ጋብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ታላቅ ኃጢአት ሆኖ ባይቀርብም፥ በማንኛውም መንገድ እግዚአብሔር ያልደገፈው ተግባር መሆኑ ጥርጥር የለውም። ከአንድ በላይ ጋብቻ ክርስቲያናዊ ካልሆነ፥ አመለካከቱ የሰውን ምኞቶች ለማርካት የተዘጋጀ ሰው ሠራሽ ክንውን ነው። በመሆኑም፡ ለሕይወት ለሚያስፈልጉ ነገሮች እግዚአብሔርን በመተማመን በመንፈስ ከመመላለስ ይልቅ በሥጋ መመላለስን ይወክላል። መጽሐፍ ቅዱስ ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደማይቻል ይናገራል (ዕብ. 11:6)።

እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ እንደሚሰጠው ቃል ገብቶለት ነበር (ዘፍጥ. 15:2-4)። ይሁንና፥ አብርሃም ባለቤቱ ሣራ መካን መሆኗን እንዳየ፥ ሣራ ከግብፃዊቷ ሠራተኛዋ ከአጋር ልጅ እንዲወልድ ያቀረበችለትን አሳብ ለመቀበል ወሰነ (ዘፍጥ. 16:1-3)። ስለ ሆነም፥ አብርሃም ከባህላዊ አፍሪካ ጋር ለሚመሳሰሉ ምክንያቶች ሌላ ሚስት ወሰደ። ከዚያን ጊዜም ጀምሮ በአብርሃም ቤት ውስጥ ሰላም አልነበረም። የእግዚአብሔር ዕቅድ በተአምራዊ ሁኔታ እንጂ በሁለተኛ ሚስት በኩል ልጅ መስጠት አልነበረም (ዘፍጥ 17:15-19)። ከአጋር ልጅ የመውለድ መጥፎ ውጤቶች አብርሃም ከሞተ በኋላም ለረዥም ጊዜያት ቀጥለዋል። ዛሬ በእኛ ዘመን እንኳን በዓረቦችና በአይሁዶች መካከል የሚታየው ግጭት እንደ ቀጠለ ነው። ብዙ ጋብቻ መፈጸም የእግዚአብሔር ዕቅድ ወይም የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ አስደግፎ መሟገት አይቻልም።

በአፍሪካም፥ ከአንድ በላይ ጋብቻን በመደገፍ ከቀረቡት የመከራከሪያ ነጥቦች ባሻገር፥ ከአንድ በላይ ጋብቻ መጥፎ ውጤቶች ከትውልድ ትውልድ በመቀጠል ላይ ናቸው። ከአንድ በላይ ከሆነ ጋብቻ በተሳሰሩ ቤተሰቦች፥ ሚስቶችና ልጆች መካከል የሚታየው የስሜት ሥቃይ፥ ቅንዓትና ውድድር፥ የዚህ ዓይነቱ ጋብቻ የግል ፍላጎትን ለማርካት የታቀደ የመሆኑን እውነት ይገልጻል። ከአንድ በላይ ጋብቻ እግዚአብሔር ሚስት የባሏን ያልተከፋፈለ ፍቅርና አትኩሮት በመቀበል የስሜትን ምልዓት እንድታገኝ የወጠነውን ዕቅድ ያከሽፋል።

አንዳንድ ለዘብተኛ የሥነ–መለኮት ምሁራን፥ የብዙ ጋብቻ ለአፍሪካ ባህል አስፈላጊ ማስተናገጃ እንደ ሆነ ያስባሉ። ለዚህ አሳብ በሚሰጠው ምላሽ፥ የብዙ ጋብቻን በመደገፍ የሚቀርቡ ባህላዊ ምክንያቶች ክርስቲያናዊ ያልሆኑ እሴቶች እንደሚያስተናግዱ ማመልከቱ ተገቢ ነው። ክርስትያናዊ ያልሆኑ ባህላዊ እምነቶች የእግዚአብሔርን ፍርድ እንጂ በረከት አያመጡም። ለምሳሌ ክብርን መሻት በባህሉ የተደገፈ ቢሆንም፥ እንደ እውነቱ ግን እግዚአብሔር ለሚጠላው የትዕቢት ኃጢአት መጋለጥ ነው (ምሳሌ 16:5፤ 21:4)። ወደፊት በሚመጡት ትውልዶች ዘንድ ስለ አንድ ሰው ስም መቀጠልም ተመሳሳይ አሳብ መናገር ይቻላል። ባህላዊ የአያት ቅድማያት እምነቶች ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ ካለው እምነት ያርቃሉ እንጂ አያቀርቡም። የጥሎሽን ገንዘብ መቀበልም ራሱ ሌላው

እግዚአብሔር የሚጠላው የስግብግብነት ኃጢአት ነው (ኢሳ. 57:17፤ ማቴ. 23:25)።

ጋብቻን ለመደገፍ የቀረቡት አብዛኞዎቹ የመከራከሪያ ነጥቦች፥ ክርስቲያናዊ ባልሆነ አመለካከት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ሰፊ ቤተሰብ መመሥረት በረከት እንደ ሆነ የሚያስረዳ አሳብ ቢኖርም በመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ መገለጽ ብርሃንነት መታየት አለበት። አዎን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ሰፊ ምድራዊ ቤተሰብ በረከት ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል [መዝ. (127):4-5]። ይሁንና፥ ይህ በረከት ሰዎች እግዚአብሔር ለጋብቻ ያቀደውን ፈቃድ ሲያበላሹ የሚመጣ አይደለም። በረከት ባሎች ተጨማሪ ሚስቶችን በማግባት የሚስቶቻቸውንና የልጆቻቸውን አንድነትና ሰላም ሲያደፈርሱ የሚመጣ አይደለም። ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣውንና በሁኔታ የማይገደበውን በረከት የሚያስገኘው ማኅበረሰብ ሰፊ ምድራዊ ቤተሰብ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ሰፊ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆነው ማለትም ቤተ ክርስቲያን ነው።

ግብረ-ገብነትን በማሻሻል ላይ የተመሠረተው የመከራከርያ ነጥብ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነው። በእርግጥ ምግባረ ብልሹነት ስሕተት ነው! ይሁንና፥ ብዙ ጋብቻ መፈጸም ለችግሩ እግዚአብሔር የሰጠው መፍትሔ አይደለም። መፍትሔው በአንድ ባልና በአንዲት ሚስት መካከል የሚፈጸም መደበኛ ወሲባዊ አንድነት ነው። ሚስት ይህንን አሳብ ከተቃወመች፥ ባል ከቤተክርስቲያን መሪዎች ወይም ከሕክምና አዋቂዎች ማስተዋል የታከለበትን ምክር ሊጠይቅ ይገባዋል። ዝሙትን በተመለከተ ባጠቃላይ እውነታው አንድም ሆነ ብዙ ሚስቶች ቢኖሩአቸው አያሌ ወንዶች ዝሙት መፈጸማቸውን እንደሚቀጥሉ ነው። የምኞት ችግር በብዙ ጋብቻ ሊቃለል አይችልም። አንድ ሰው ዝሙት ከፈጸመ በኋላ የዝሙት ተግባሩን ሕጋዊ ለማድረግ፥ በኋላ ሴቲቱን በሚስትነት የሚወስድባቸው አያሌ ገጠመኞች አሉ። ንጉሥ ዳዊት ምንም እንኳን ብዙ ሚስቶች ቢኖሩትም፥ ይህንኑ አድርጓል! ለዚህም ለኃጢአቱ እግዚአብሔር ዳዊትን ኮንኖታል (2 ሳሙ. 11:26-27)።

ዳግም የተወለደውንና ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉትን አባወራ፥ የመጀመሪያዋን ሚስቱን አስቀርቶ የተቀሩትን እንዲፈታ መጠየቅ፥ ከአንድ በላይ ጋብቻ ለሚያስከትለው ችግር ክርስቲያናዊ መፍትሔ አይደለም። ይህ ለሚስቶቹ እንክብካቤ ለማድረግ ቃል ኪዳን ለገባው ባል ፍትሐዊ ያልሆነና ኃላፊነት የጎደለው ጠባይ ይሆናል (ዘጉ. 30:1-2፥ 16)። ይልቁንም፥ መፍትሔው እግዚአብሔር በራሱ ፍጹም መንገድ ነገሮችን

እንዲያከናውን፥ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን መጋቢዎችና ሽማግሌዎች በጸሎት መደገፍና በምክር መርዳት ነው። ሰዎችን በማያስፈልግ ሁኔታ የማይጎዳ መፍትሔ ሊያመጣ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ለጸሎት ምላሽ በመስጠት ችግሩን ሊያቃልል የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። የእግዚአብሔር መንገድ ለተግባራዊነት ብዙ ጊዜ ሊወስድ ቢችልም፥ መፍትሔዎቹ ሁልጊዜም ርኅራኄና ፍጹምነት የተካተተባቸው ናቸው። ብዙ ሚስቶች ያሉት ሰው ላለበት ሁኔታ የእግዚአብሔርን ምላሽ ያገኝ ዘንድ ጸሎትና ትዕግሥት ብቸኛ መንገዶቹ ናቸው።

ከአንድ በላይ ጋብቻ ከመፈጸም ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለማቃለል በጣም ከባድ ነው። ይህም ገና ሳላገቡት ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይገባል። ለወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶችን መውሰድ ትልቅ ስሕተት ነው።

ብዙውን ጊዜ ወደ ክርስቶስ የተመለሰ ባለ ብዙ ሚስቶች ግለሰብ ጥምቀት መውሰድ ይኖርበት እንደ ሆነ ይጠየቃል። ለጥያቄው ምላሽ የሚሰጠው ስለ ጥምቀት ፍች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ከማገናዘብ ነው። ጥምቀት አንድ ሰው የክርስቶስ አካል ክፍል እንደ ሆነ የሚያመለክት ይፋዊ ምስክርነት ነው። ወደ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት ዘማዊ፥ አመንዝራ ወይም ሌባ ለነበረ ሰው ጥምቀትን እንከለክል ይሆን? በፍጹም አይከለከልም (1 ቆር. 6:9-11)። እንዲህ ዓይነት ግለሰቦች ሁሉ እውነተኛ ንስሐ ገብተው በክርስቶስ ካመኑ፥ አዲስ ፍጥረት ናቸውና ሊጠመቁ ይገባል (2 ቆር. 5:17)። የባለ ብዙ ሚስቶችም ሁኔታ ከዚህ የተለየ አይደለም። አንድ ሰው ከኃጢአቱ ንስሐ ገብቶ ክርስቶስን ጌታውና መድኃኒቱ አድርጎ ሲቀበል፥ ከአንድ በላይ ጋብቻን ጨምሮ የቀደሙ ኃጢአቶች ሁሉ ይቅር ይባላሉ (ቆላ. 2:13፤ 1 ዮሐ. 2:12)።

ምንም እንኳን የውኃ ጥምቀት ሊወስድ ቢችልም፥ ብዙ ሚስቶች ያሉት ሰው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከቶውንም ሽማግሌ ወይም ዲያቆን ሊሆን አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ የማይነቀፍ፥ የአንዲት ሚስት ባል» (1 ጢሞ. 3:2)። በኋላም ሐዋርያው፤ «ዲያቆናት . . . እያንዳንዳቸው የአንዲት ሚስት ባሎች ይሁኑ» ብሏል (1 ጢሞ 3:12)። ይህም የሆነው እግዚአብሔር በጋብቻ አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት የሚለው ዕቅድ በቤተክርስቲያን መሪዎች ሕይወት በትክክል እንዲታይ ስለሚፈልግ ነው።

ከደኅንነት በኋላ ያለው ከአንድ በላይ ጋብቻ ጉዳይ በጣም የተለየ ነው። ከአንድ በላይ ጋብቻ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስላልሆነ፥ ለክርስቲያን

ሁለተኛ ሚስት ማግባት በግልጽ የዓመፅ ተግባር ነው። ይህ ኃጢአት ስለ ሆነ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ልታስወግደው ይገባል። እግዚአብሔር ለአንድ ወንድ አንዲት ሚስት ብቻ እንድትኖረው ይፈልጋል። ሁለተኛ ሚስት የሚያገባ ክርስቲያን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀጣ ይገባል (1 ቆሮ. 5:11-13)።

## ረ. እግዚአብሔር ስለ ፍች ምን ይላል?

ከአንዲት ሚስት በላይ ማግባት ሕጋዊ ባልሆነባቸው አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ፥ ዝሙትና አመንዝራነት ወደ ፍች ይመራል። ብዙውን ጊዜ የተፋቱት ሰዎች ከዝሙት ሸርኮቻቸው ጋር ይጋባሉ። በአንድ ጊዜ በአንድ ቤት ውስጥ የተለያዩ ሚስቶችን ካለማስተናገዱ በቀር፥ ይህ ከአንድ በላይ ጋብቻ ጋር የሚመሳሰል ነው። ይሁንና፥ ብዙውን ጊዜ ፍች ከብዙ ጋብቻ በላይ ለተጎዳው ባል ወይም ሚስት የስሜት ሥቃይን ያስከትላል! ይህም የሚሆነው ባል ወይም ሚስት ሌላ ሰው በመምረጥ የቀድሞ ፍቅራቸውን ስለሚተው ነው። ፍች ለልጆችም ከፍተኛ ሥቃይ ነው።

እግዚአብሔር ፍችን ይጠላል (ሚል. 2:16)። ፍች እግዚአብሔር ለጋብቻና ለቤተሰብ የወጠነውን ዕቅድ ያጠፋል። የወላጆቻቸው ፍቅር ወደ ጥላቻ ሲመለስና በመጨረሻም ሲፋቱ የሚመለከቱ ልጆች በሕይወታቸው በጥልቀት ይጎዳሉ። ብዙውን ጊዜ በጋብቻ ላይ መራራና አሉታዊ አመለካከት ሲኖራቸው፥ በሁሉም ሰው ይበሳጫሉ። በቤት ውስጥ ፍች ሲካሄድ ይበልጥ የሚጎዱት ልጆች ናቸው። ልጆች የዚህ ዓይነት ዝቅተኛ የጋብቻ አመለካከት ስለሚኖራቸው፥ በወላጆቻቸው የተመለከቱትን ተመሳሳይ ዝሙትና ፍች ይደግማሉ።

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ፍችን ቢጠላም፥ ፍች እንደሚፈጸም ያውቃል። ከሰዎች ጋር ባሉበት ስፍራ ሁሉ ይገናኛል። ሌሎችን ኃጢአቶች ይቅር እንደሚል ሁሉ እግዚአብሔር ይህንንም ኃጢአት ይቅር ይላል [መዝ. (103):3]።

ፍች በዓለማችን በተለይም በትላልቅ ከተሞች ከፍተኛ ችግር በመሆን ላይ ይገኛል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ጋብቻን የዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን ለማድረግ የሚፈቅዱ ሰዎች በጣም ጥቂት ናቸው (ማቴ. 19:6)። በአሁኑ ጊዜ በሰሜን አሜሪካ፥ ፍች ከዕድሜ ልክ ጋብቻ ይበልጥ እየተዘወተረ መጥቷል። የዚህ ዘይቤ ውጤት በአፍሪካ ሁሉ በመዘውተር

ላይ ይገኛል፤ ይህም የሆነው ብዙ አፍሪካውያን በዝሙትና ፍች የተሞሉትን የአሜሪካ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ስለሚመለከቱ ነው።

ብዙውን ጊዜ ወጣቶች ከቤተሰብ አካባቢ ሲርቁ፣ ሥነ-ምግባራዊና መንፈሳዊ እሴቶቻቸውን ያጣሉ። በመሆኑም፣ ወሲባዊ ግድፈትንና ዝሙትን ሊፈጽሙ ይችላሉ። እነዚህ ደግሞ ጋብቻን ለፍች የሚዳርጉ ኃጢአቶች ናቸው።

የትዳር ጓደኛው ታማኝ ሳይሆንለት ሲቀር እግዚአብሔር ሰው ምን እንዲያደርግ ይፈልጋል? እግዚአብሔር ሰዎች እርስ በርሳቸው ይቅር እንዲባባሉ ይፈልጋል (ቆላ. 3:13)። ንስሐ መግባት፣ ይቅርታና የፈራረሱትን የሰው ልጆች ግንኙነቶች ማደስ፣ ሁልጊዜም የእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ ነው። ጴጥሮስ ኢየሱስን፣ «ጌታ ሆይ፣ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው፤ ኢየሱስ እንዲህ አለው፡- እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም» (ማቴ. 18:21-22)። ይህ የይቅርታ መመሪያ በሆሴዕ ሕይወት ውስጥ ሊታይ ይችላል። ምንም እንኳ ጋለሞታ ብትሆንና ብዙ ጊዜም ሆሴዕን ብትከዳውም፣ እግዚአብሔር ታማኝ ያልሆነች ሚስቱን ጎሜርን ዳግም እንዲወስዳት ነግሮታል (ሆሴ. 3:1-3)።

ችግሮች በጋብቻ ውስጥ

በጋብቻ ውስጥ ታማኝነትን ከማጉደል በተጨማሪ፣ ሌሎችም ብዙ ችግሮች አሉ። ከሁሉም የሚልቁ ችግሮች የሚከሰቱት በመዋለ ንዋይ አለመስማማት፣ ለተስፋፋው ቤተሰብ (ዘመድ አዝማድ) በሚሰጥ ታማኝነት ውጥረት፣ በባህላዊ ልዩነቶችና በነገሮች ላይ ካለመወያየት ነው። አብዛኞዎቹ የጋብቻ ችግሮች ሁለት ገጽታዎች አሉአቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘው አስገራሚ ጥቅስ፣ «በአደባባይ በመጀመሪያ ቀርቦ የሚናገር ሰው፣ ተከራካሪው መጥቶ ጥያቄ እስኪያቀርብለት ድረስ፣ ዘወትር እርሱ ብቻ ትክክል የሆነ ይመስለዋል» ይላል (ምሳሌ 18:17 – ከ1980 ዓ. ም. አዲስ ትርጉም)። ይህ በብዙ የጋብቻ ክርክሮች ውስጥ እውነት ነው። አንደኛው በትዳር ጓደኛው እጅግ እንደ ተበደለ አድርጎ ሊያስብ ይችላል። ይሁንና፣ ጠቅላላው ታሪክ ሲገለጽ መልካም መስተንግዶ ያልተደረገለት ሰው ሌላውን ፍቅር በመንፈግ፣ በሚጎዱ ቃላት ወይም በጭካኔ ባሕርይ ይጎዳዋል።

የጋብቻን ችግር ለመፈውስ የሚረዳ መድኃኒት አለ። ይህም መድኃኒት ሁለት ክፍሎች አሉት። ሁለቱ ክፍሎች ፍቅርና ይቅርታ ይባላሉ። ምሳሌ 10:12፥ «ፍቅር ግን ኃጢአትን ሁሉ ትከድናለች» ይላል። ቆላስይስ 3:13-14፥ «ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ፤ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፤ በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት» ይላል።

## ሰ. የትዳር ጓደኛ ስለ መምረጥ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች ምንድን ናቸው?

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ከቀረበው ታሪክ ውስጥ፥ የትዳር ጓደኛን ስለ መምረጥ አንዳንድ ጠቃሚ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች እናገኛለን። የአብርሃም ዋንኛ የቤቱ አለቃ የነበረው ኤልዔዘር፥ ከአብርሃም በተቀበለው ትእዛዝ መሠረት ለይስሐቅ ሚስት ሊፈልግለት መጣ። ኤልዔዘር በሳል ሰው ነበር። አንዲት ሚስት ሊኖራት የሚገባት ዋንኛ ነገር መልካም ባሕርይ እንደ ሆነ ያውቅ ነበር። ኤልዔዘር እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ ያምን ነበር። በጣም በጣም ማስተዋል የታከለበት ጸሎት አቅርቦአል። በጸሎቱም፡ «ውኃ እጠጣ ዘንድ እንስራሽን አዘንብዪ የምላት እርስዋም፡- አንተ ጠጣ፥ ግመሎችህንም ደግሞ አጠጣለሁ የምትለኝ ቆንጆ፥ እርስዋ ለባሪያህ ለይስሐቅ ያዘጋጀሃት ትሁን» ብሏል (ዘፍጥ. 24:14)።

የኤልዔዘር ጸሎት እግዚአብሔር ተባባሪ፥ ረጂ፥ ለጋስና ትጉ ሠራተኛ ወደ ሆነች ልጅ እንዲመራው የጠየቀበት ነበር። እነዚህ ብቃቶች የሌላት ልጅ «ውኃ አጠጪኝ» ስትባል ለግመሎች ጭምር ለመቅዳት እንደማትፈልግ ግልጽ ነው። ርብቃ ግመሎቹ ገና ከሩቅ አገር መድረሳቸው እንደ ሆነ ታውቅ ነበር። ግመሎች ብዙ ውኃ ስለሚጠጡ፥ ጥማታቸውን ለማርካት አድካሚ ሥራ ሳይጠይቅ አልቀረም። ኤልዔዘር ለይስሐቅ ሚስት ሲፈልግ የሚከተሉትን መመሪያዎች ተጠቅሟል፡-

1. ከሕዝቦች መካከል የአብርሃም ዓይነት እምነት የነበራት ልጅ ፈለገ። የማያምኑትን ሴቶች ለመምረጥ አልፈለገም ነበር (ዘፍጥ. 24:3)።
2. በጸሎት የእግዚአብሔርን ምሪት ፈለገ (ዘፍጥ. 24:12-14)።
3. ግሩም ባሕርይ ያላትን ልጅ ፈለገ (ዘፍጥ. 24:14)።

4. በባህል ከአብርሃም ጋር ከሚቀራረቡ ሰዎች ሚስት ፈለገ (ዘፍጥ. 24:3-4)።

5. እግዚአብሔር ለይስሐቅ ልዩ ሴት እንዳዘጋጀለት ያምን ነበር (ዘፍጥ. 24:14)።

6. እግዚአብሔር ወደ ትክክለኛዋ ልጅ እንደሚመራው ያምን ነበር (ዘፍጥ. 24:14)።

7. በሁኔታዎች ውስጥ የጸሎቱን መልስ በንቃት ይጠብቅ ነበር (ዘፍጥ. 24:17-21)።

መልካም የትዳር ጓደኛ ለመምረጥ ሌሎችም አስፈላጊ መሥፈርቶች አሉ። እነዚህ ተመሳሳይነት በሚለው ቃል ሊጠቃለሉ ይችላሉ። ከሚያገባው ሰው ጋር ይበልጥ ተመሳሳይነት ያለው ሰው፥ ብዙም ለማስተካከል የሚቸግረው ነገር አይኖረውም።

ከሌላ ነገድ፥ ከሌላ ብሔር፥ ከሌላ ቋንቋ ወይም ከሌላ ዘር ጋብቻ መመሥረት ኃጢአት አይደለም። ይሁንና፥ በሁለቱ የተለያዩ ባለ ትዳሮች መካከል ከእነዚህ ዓይነት ልዩነቶች አንድ ወይም ከዚያ የሚበልጥ ነገር ካለ፥ ተስማምቶ መኖሩ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተገለጸውን ዓይነት አንድነት ለማግኘት፥ ባልና ሚስት ከተመሳሳይ ባህሎችና እሴቶች ቢመጡ መልካም ነው። ከመንፈሳዊ ጋብቻ አስፈላጊ ዓላማዎች አንዱ በአንድ አሳብ መስማማት ነው (ፊልጵ. 2:2)። በትዳር ጓደኛሞች መካከል ከፍተኛ ልዩነት ካለ፥ በአንድ አሳብ መስማማቱ ከባድ ሊሆን ይችላል። አብርሃም ኤልዔዘርን ከራሱ ወገን ለይስሐቅ ሚስት እንዲፈልግ በመጠየቁ የጥበብ ተግባር አከናውኗል (ዘፍጥ. 24:3-4)።

የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሰዎች ቢጋቡ ምን እንደሚፈጠር አስብ። እርስ በርሳቸው ሊግባቡ የሚችሉት ለአንዳቸውም ልብ በማይደርስ ሦስተኛ ቋንቋ ነው። ይህም ካልሆነ አንደኛው የሌላውን ቋንቋ የግድ በሚገባ ማወቅ አለበት። እነዚህ መፍትሔዎች ሁለቱም ከሁሉም የተሻለ ዓይነት ግንኙነት አይፈጥሩም። በጋብቻ ወቅት ከማንኛውም ሌላ ሰብአዊ ግንኙነት በላይ፥ በጋብቻ እርስ በርስ በአሳብ መረዳዳትና ወደ ልብ ዘልቆ በሚሰማ ሁኔታ አሳብን መግለጽ አስፈላጊ ነው።

አንድነትን ለመጠበቅ ከሚያስቸግሩት ሌሎች ልዩነቶች መካከል አንዳንዶቹ፥ የተለያዩ የሕይወት ዓላማዎች፥ ሰፊ የዕድሜ ልዩነት (በተለይም ሴቲቱ በብዙ የዕድሜ ልዩነት የገፋች ከሆነች)፥ የትምህርት

ደረጃ ልዩነት (በተለይም ሚስት በትምህርቷ ከበለጠች)፥ በገንዘብ ላይ የሚኖር የተለያየ አመለካከት፥ የባሕርይ (ሰብእና) መለያየት ናቸው። ይህም ሆኖ፥ እነዚህ ልዩነቶች ካሉ ጋብቻ መፈጸም አይቻልም ማለት አይደለም። ይልቁንም፥ በባልና ሚስት መካከል አያሌ ግዙፍ ልዩነቶች ካሉ፥ አንድነት ያለው ግንኙነት ለመመሥረት የበለጠ መትጋት ይኖርባቸዋል።

## ፮. ክርስቲያን ባለትዳሮች የመካንነትን ችግር እንዴት ይወጣሉ?

ጆንና ባለቤቱ ሊድያ በእምነት ከፍላቸው በመጋቢነት ጌታን ለማገልገል የሚፈልጉ የተሰጡ ክርስቲያኖች ነበሩ። ጆን በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ተማሪ ነበር። እርሱና ባለቤቱ ልድያ ለ12 ዓመታት በጋብቻ ተሳስረው የቆዩ ሲሆን፥ ምንም ልጅ አልወለዱም ነበር። የጆን ጎረቤቶች ልድያ የሌላ ነገድ አባል በመሆኗ እንዳያገባት ጆንን ብዙ ጊዜ አስጠንቅቀውት ነበር። በኋላም እርግማን ያለባት በመሆኑ፥ ልድያ ልጅ እንደማትወልድ ያስገነዝቡት ጀመር። እያንዳንዱ ዓመት ባለፈ ቁጥር፥ ልድያ የበለጠ ስትጨነቅ፥ ጆንም ይበልጥ ቁጡና ተናዳጅ እየሆነ መጣ። እስቲ አንተስ ከእግዚአብሔር ቃል ጆንንና ልድያን እንዴት ትመክራቸዋለህ? ክርስቲያን ባለትዳሮች የመካንነትን ችግር እንዴት ሊወጡት ይገባል?

በአፍሪካ ብዙው የልጅ አልባነት ስሜታዊ ሥቃይ ከባህላዊ የልጅ እሴት ጋር የተያያዘ ነው። ከእነዚህም እሴቶች አንዳንዶቹ የክርስቲያን አሳቦች አይደሉም። ብዙዎቹ የአፍሪካ ባህሎች በጣም ጠንካራ የማኅበረሰብ ስሜት አላቸው። ልጆች ለአንድ ሰው ቤተሰብ መቀጠልና በመንፈሳዊ ዓለም ለሚኖረው ትውልዳዊ ደረጃ አስፈላጊዎች እንደ ሆኑ ይታመናል። በአንዳንድ ባህሎች እነዚህ እሴቶች በጣም አስፈላጊዎች በመሆናቸው ባል ወንድ ልጅ እስኪያገኝ ድረስ ልጅ እንደሌለው ይናገራል።

በአንዳንድ ባህሎች፥ ዘላለማዊ ሕይወት ማለት ፍጻሜ የሌለው የአንድ ሰው የቤተሰብ ሐረግ ቅጥያ ማለት እንደ ሆነ ይታመናል። በእንደዚህ ዓይነት ባህሎች፥ ልጅን መውለድ ሃይማኖታዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል። እንዲህ ዓይነት ባህሎች ባለትዳሮች ልጅ ካልወለዱ በእግዚአብሔር የተረገሙ እንደ ሆኑ ያምናሉ። እነዚህ ስለ ልጅ አልባነት የሚቀርቡ ባህላዊ አሳቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኙም። ይሁንና፥ ከእንደዚህ ዓይነት ማኅበረሰብ የሚመጡ ክርስቲያኖች እውነቱን ሳይገነዘቡ በሕዝባቸው እምነት ሊለወጡ ይችላሉ። ልጅ በማይወልዱበት ጊዜ መራራና ቁጡ የሚያደርጋቸው ይኸው ተጽዕኖ እንጂ የእግዚአብሔር ቃል

የሚያስተምረው እውነት አይደለም። ባለትዳሮቹ ጌታን በታማኝነት ለመከተል የሚፈልጉ ከሆነና በሕይወታቸውም ውስጥ የተሰወረ ኃጢአት ከሌለ፥ በእግዚአብሔር ተረግመዋል ማለት አይደለም። እንደዚህ የመሳሰሉ ገጠመኞች ሲኖሩ፥ ክርስቲያን ባለትዳሮች በሕዝባቸው ባህላዊ እምነቶች ላይ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ቃል ዘላለማዊ እውነት ላይ መደገፍን መማር አለባቸው። እነዚህ ሁለት የእምነት መንገዶች፥ የልጅ አልባነትን ጉዳይ በጣም በተለያየ ሁኔታ ይመለከታሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ እንደ ሆኑ ይናገራል [መዝ. (127):3]። ይሁንና፥ ልጅ አለመውለድ በእግዚአብሔር መረገም እንደ ሆነ የሚናገረው አሳብ ሐሰት ነው። በተጨማሪም፥ ዘላለማዊ ሕይወትን ልጅ ከመውለድ ጋር ማያያዝ ክርስቲያናዊ ያልሆነ አሳብ ነው። ለብዙዎቹ ሰዎች እግዚአብሔር የልጆችን ስጦታ ይሰጣል። ይሁንና፡ እግዚአብሔር ልጅ የሚነፍጋቸው ሰዎች አሉ፤ ይህም የሚሆነው፥ ለእነርሱ ልጅ መውለድ በረከት እንደማይሆን ስለሚያውቅ ነው። መዝሙር (84):11፥ «እግዚአብሔር አምላክ ምሕረትንና እውነትን ስለ ወደደ፥ ሞገስንና ክብርን ይሰጣል፤ እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን ከመልካም ነገር አያሳጣቸውም» ይላል።

ሌላው ሰው እንደ ረገማቸው የሚያምኑበት ምክንያት ካላቸው፥ ክርስቲያን ባለ ትዳሮች እንዲህ ዓይነቱን እርግማን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የማፍረስ ሥልጣን አላቸው (ሉቃ. 10:19፤ 1 ዮሐ. 4:4)። በሁሉም ሁኔታ ውስጥ፥ እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው በጸሎት ሊጠይቁ ይችላሉ። ይስሐቅ ልጅ ላልነበራት ሚስቱ ለርብቃ ያደረገው ይህንኑ ነበር (ዘፍጥ. 25:21)። ልጅ ያልነበራት የሕልቃና ሚስት ሐናም ያደረገችው ይህንኑ ነበር (1 ሳሙ. 1:10-16)።

ከጸለዩም በኋላ እግዚአብሔር አሁንም ለክርስቲያን ባለትዳሮች ልጅ ከከለከለ፥ እርሱ ምክንያት አለው። ምናልባት ለእነዚህ ሰዎች ልጅ መውለድ መልካም እንደማይሆን ስለሚያውቅ ይሆናል። ምናልባትም ሚስት በወሊድ በመሞት የባሏን ልብ እንደምትሰብር ስለሚያውቅ ይሆናል። ለእነዚህ ሰዎች የሚወለደው ልጅ ታሞ እንደሚሞት፥ የከፋ በሽታ እንደሚኖርበት ወይም አካለ-ስንኩል እንደሚሆን ስለሚያውቅ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ልጆቹን አላስፈላጊ ከሆነ ሕመምና ሥቃይ ለመጠበቅ ስለሚፈልግ፥ ለሚጸልዩ መንፈሳዊ ባለትዳሮች ልጅ ሊነሣቸው ይችላል። እግዚአብሔር ልጅን የማይሰጥባቸው ሌሎችም ምክንያቶች

ሊኖሩ ይችላሉ። እግዚአብሔር ልጅ ከከለከላቸው ባለትዳሮች ምን ማድረግ አለባቸው?

ምናልባት እግዚአብሔር ልጅ የከለከላቸው ወላጅ የሌለውን ልጅ እንዲያሳድጉ ስለሚፈልግ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለመበለትና ወላጅ ለሌላቸው ልጆች እንደሚራራ ብዙ ይናገራል (ዘዳ. 14:29፤ 24:19-21)። ባለትዳሮች ከአብራካቸው የወጡ ልጆች ካሉአቸው፥ ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ለማሳደግ አያስቡም ይሆናል። በአንዳንድ ባህሎች፡ ከባህላዊ እምነቶች ሳቢያ መንታዎች ክፉ እንደ ሆኑ ይታመናል። በእነዚህ ማኅበረሰቦች ውስጥ መንታ ልጆች ሲወለዱ፥ አንድም መገደል አሊያም መጣል ዕጣ-ፈንታቸው ይሆናል። ክርስቲያን ባለትዳሮች የተጣለውን ልጅ በመውሰድና ክርስቲያናዊ ቤት በመስጠት ግሩም ክርስቲያናዊ አገልግሎት ሊያበረክቱ ይችላሉ።

ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ ሚሲዮናዊ ዶክተርና ባለቤቱ አካለስንኩላን ልጆች ለማሳደግ ወሰኑ። በዚህም መሠረት ሦስት ልጆች አሳደጉ። ለእነዚህም ልጆች አፍቃሪ ክርስቲያናዊ ቤት ሰጡአቸው። ሌላው ሚሲዮናዊ ዶክተር በከተማ ውስጥ ከሚገኝ የቆሻሻ መጣያ ያልተፈለገችውን ልጅ አተረፈ። ለዚህች ልጅ አፍቃሪ ክርስቲያናዊ ቤት ሰጥተው ስላሳደጉአት፥ አሁን ከዩኒቨርስቲ ተመርቃለች። ለልጅ አልባነት ማደጎ በጣም ግሩም ክርስቲያናዊ መፍትሔ ነው።

## ማጠቃለያ

ጋብቻ በዓለም ባህሎች ሁሉ ውስጥ በተለያየ መልኩ ይከናወናል። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ፥ ጋብቻ የመጀመሪያው የሰው ማኅበራዊ ተቋም ነው። የሰውን ልጅ ወንድና ሴት አድርጎ በፈጠራቸው ጊዜ፥ ጋብቻን ያቀደውና የመጀመሪያውን ጋብቻ ያከናወነው ራሱ እግዚአብሔር ነበር። ለሰዎች ሁሉና በዓለም ለሚገኙ ባህሎች ሁሉ፥ እግዚአብሔር የወጠነው የጋብቻ ዕቅድ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር አንድ ወንድ አንዲን ሴት ለሕይወት ዘመን የታማኝነት፥ የፍቅር፥ የኅብረት፥ የብርታት፥ የድጋፍ፥ የደስታና የጋራ እርዳታ ቃል ኪዳን በመግባት እንዲያገባት ዐቅዷል። እንደ ብዙ ጋብቻ ያሉ ሌሎች የጋብቻ ዓይነቶች የሰው አሳብ እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሌላቸው ናቸው። ፍች እግዚአብሔር ሰው በጋብቻ ውስጥ እንዲያገኘው ያቀደውን ፍጹም ደስታ ስለሚያጠፉ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው። በጋብቻ ቃል ኪዳን ውስጥ ወሲብ ቅዱስ፥ ንጹሕና በእግዚአብሔር

የተባረከ ነው። ወሲብ እግዚአብሔር የልጆችን በረከት የሚገልጽበትና ለሚስቶችና ለባሎች የእርካታ መሣሪያ ነው። እንደ ዝሙትና አመንዝራነት ያሉ ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸሙ ወሲባዊ ግንኙነቶች ሁሉ የከፉ ኃጢአቶች በመሆናቸው፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያስከትላሉ።

ጋብቻ የተሳካ ሊሆን የሚችለው ባሎችና ሚስቶች የመጽሐፍ ቅዱስን ትእዛዛት በመከተል፥ እግዚአብሔር ለጋብቻ የወጠነውን ዕቅድ ሲፈጽሙ ነው። ሚስቶችን በመምራቱ በኩል ለባሎች ምሳሌ የሚሆነው ክርስቶስ ራሱ ነው (ኤፌ. 5:23)። ለባሎች በመገዛቱ በኩል ሚስቶች ሊከተሉት የሚገባው ምሳሌ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ያላት ግንኙነት ነው (ኤፌ. 5:24)። ባሎች ሚስቶቻቸውን ልክ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚወዳት አድርገው እንዲወዱአቸው ታዝዘዋል (ኤፌ. 5:25)። ይህ የአገልጋይነት፥ መሪነትና ራስን የመሠዋት ፍቅር ነው። ሚስቶች ለባሎቻቸው ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ በምትገዛው መልክ እንዲገዙ ታዝዘዋል (ኤፌ. 5:24)። የዚህ መገዛት ምሥጢሩ ለክርስቶስ ብሎ መፈጸሙ ነው። ልጆችን በማሳደጉ በኩል ወላጆች ሊከተሉት የሚገባው ምሳሌ፥ ሰማያዊ አባታችን በመሆን የሚወደን፥ የሚያስፈልገንን የሚያሟላልን፥ የሚመራን፥ የሚያስተምረንና የሚጠብቀን እግዚአብሔር አብ ነው (ኤፌ. 5:1-2)። እነዚህ ኃላፊነቶች ሙሉ ለሙሉ ሊከናወኑ የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ አማካኝነት ነው።

ልጆች በጋብቻ ውስጥ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ቢሆኑም፥ ልጅ አለመውለድ ግን ባለትዳሮቹ በእግዚአብሔር እንደ ተረገሙ አያመለክትም። ይህ አሳብ የመጣው ክርስቲያናዊ ካልሆኑ ሃይማኖቶች የሐሰት ትምህርት ነው። ልጅ በመውለዱ በኩል ችግር ካለ፥ ባለትዳሮቹ ሐኪም ማማከር አለባቸው። ልጅ ለሌላቸው ባለትዳሮች ልጅ የመውለድን ዕድል የሚያሰፉ ውጤታማና ጎጂ ያልሆነ የቤተሰብ ምጣኔ ብልሃት አለ። አራርቆ ለመውለድም ተመሳሳይ መንገድ መጠቀም ይቻላል። እግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ ልጅ ከከለከለ፥ ባለትዳሮቹ በእግዚአብሔር ምሪት የማደጎ ልጅ ሊፈልጉ ይችላሉ።

## በምዕራፍ 16 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. ከእግዚአብሔር ዕይታ አንጻር ፍጹም ጋብቻን እንዴት ትገልጸዋለህ? መልስህን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አስደግፍ።

2. ቡድኑ ፍጹም ጋብቻ ምን እንደ ሆነ ያብራራ። ከዚያም በትናንሽ ቡድን ተከፋፍላችሁ፥ ይህንን ፍጹም ጋብቻ ለመፍጠር ሁለቱም ባልና ሚስት ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ተወያዩ። እያንዳንዱ ቡድን ለባሎችና ለሚስቶች የሚሆኑትን ነገሮች መዘርዘር አለበት።

3. ባል ከሚስቱ ጋር ሊሠራ የሚችላቸውና አእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነታቸውን ለማጠናከር የሚረዱ ነገሮች ምንድን ናቸው?

4. እግዚአብሔር ለምን ፍችን እንደሚጠላ አብራራ።

5. አራት አባላት በሚገኙባቸው ትናንሽ ቡድኖች ተከፋፈሉና በ 1ኛ ጴጥሮስ 3:7 እንደ ታዘዘው፥ ባሎች ሚስቶቻቸውን ሊያከብሩ በሚችሉባቸው መንገዶች ላይ ተወያዩ።

6. ባል ከሚስቱ ጋር የሚኖረውን መንፈሳዊ አንድነት ሊያጠናክር የሚችል ምን ተግባር ሊፈጽም ይችላል?

7. ዝሙት ለምን እንዲህ የከፋ ኃጢአት እንደ ሆነና፥ በጋብቻ ላይ ምን እንደሚያስከትል ግለጽ።

8. ጵርስቅላና አቂላ በሐዋርያት ሥራ 18 እና በአንዳንድ የጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ የተጠቀሱ ባለትዳሮች ነበሩ። በሐዋርያት ሥራ 18:26 በጋብቻቸው ውስጥ የተጠቀሰው ምን ዓይነት አንድነት ነው?

9. በጋብቻ ውስጥ የወሲብ ግንኙነት እንዴት እግዚአብሔርን እንደሚያስከብር ግለጽ።

10. አንድ ወጣት ወደ አንተ ይመጣና ከአንዲት ልጃገረድ ጋር ዝሙት እንደ ፈጸመ ይነግርሃል እንበል። ልጂቱንም እንደሚያፈቅራትና ሊያገባት እንደሚፈልግ ይገልጽልሃል። ሆኖም ልጂቱ ክርስቲያን አይደለችም። ይህንን ወጣት እንዴት ትመክረዋለህ? መልስህን ለማስደገፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ስጥ።

11. ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉት ሆኖ ወደ ደኅንነት ስለ መጣ ሰው ምን እንደምትል ተናገር።

